# ግንቦት

ግንቦት ጥቁር ደመና ጥለት
የብርቅየ ልጆች የአቤቱታ ጩኸት
የሳንጃና ጥይት ምላሽ የህንባ ጅረት
ወላድ መሃን ያረገ ህለተ ሰማህት

ግንቦት ዋይታ ጭንቅ የደም ፍሰት
የሰው መሰል የቀን ጅቦች እብደት
የእብሪተኞች በትር የዘረኞች ቅዠት
ሰብህና አልባ ጭካኔ ወደር የለሽ ትምክት

ግንቦትና መዲናችን ግንቦትና አዲስ
የደም ማህተም የቃለመሃላ ጽንስ
የመብት አድማ የፍትህ ብቅል
የአምቢበል ጥሪ የትግል ደውል

የእባት ጩኸት የእናት ዕንባ
የ ደም ቀዬ የደም አምባ
መዘገበ ማህደርዋ የአዲስባ
በለጋ ሊጆችዋ የመስዋህት ደም ታጥባ

ግንቦት የቁርጥ ቀን የትግል
ለአንድነት ለነጻነት ለሃገር ሲባል
ባንዳን ሊያሳፍር ዘረኞችን ሊያጠፋ
ለዓላማው ጽናት ላይበገር ሊገፋ

ቃለ ግንቦት ግንቦት፡ ቃል
ለፍትህ፡ መረጋገጥ፡ ህብረ፡ ትግል
ለህግ፡ የበላይነት፡ ለዲሞክራሲያዊ፡ ድል
ለማይፈታ፡ አንድነት፡ ለሃገር፡ ስንል

ለአንድነትዋ፡ ለህልውናዋ፡ የረገፉ
በዘረኛ ጥይት በግፍ የተደፉ
ሕግን፡ ነጻነትን፡ አፍቅረው፡ ከነፍሳቸው
ህያው፡ ናቸው፡ ህያው፡ ናቸው፡

ብርዞ፡ ከፍራንክፈርት